# ኢስራዕና ሚዕራጅ



Scanned by CamScanner

# የመጀመሪያው ፍጡር ምንድ ነው?

የመጀመሪያው ፍጡር ውሃ ሲሆን የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል " አላህ መጀመሪያ የፈጠረው ውሃ ነው"። ውሃ ከመፈጠሩ በፊት የሰው ልጅ፣መላኢካዎችም ሆኑ ጅኖች እንዲሁም ሌሎች ፍጡራን አልተፈጠሩም። ከውሃም ሁሉ ነገር ተፈጠረ ። አላህ በቁርዓን እንዲህ ብሏል

{وجعلنا من الماء كل شيء حي}

"በውሃ ሁሉንም ነገር ህያው አደረግነው"

ህያው አደረግን ሲባል ህይወት ያላቸውን ከግዑዝ አካላት ለይቶ ለማላቅ ነው። ምክንያቱም ህያው ከሆኑ ፍጡራን መካከል ነቢያቶች እና መላኢካዎች ይገኙበታል። ቡኻሪይ እና ሌሎቹ በዘገቡት ሃዲስ የአሏህ መልክተኛን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የመጀመሪያ ፍጡር ምንድነው በማለት ሲጠየቁ «አላህ ነበር ምንም ነገር ሳይሮር፤ ዐርሽም በውሀ ላይ ነበር፤ ቀለምን ሰሌዳ ላይ ሁሉንም ነገር እንድትፅፍ አዘዛት፤ ከዚያም ሰማይና ምድርን ፈጠረ» በማለት መለሱላቸው::

ዐርሽም በውሀ ላይ ነበር ማለት ከጀነት በላይ ያለው ዐርሽ ከውሀ በኋላ የተፈጠረ ፍጡር ነው ማለት ነው::

አሏህ ነበር ምንም ነገር ሳይኖር በፊት ማለት ደግሞ አላህ ብርሀንን፣ ጨለማን፣ቦታን፣ ጊዜን፣ ዐርሽን፣ ሰማያትና ምድርን እንዲሁም በሰማይና ምድር ውስጥ ያሉ ፍጡራንን ጠቅላላ ከመፍጠሩ በፊት የነበረ ነው ማለት ነው:: ይህንንም አላህ ሱብሀነውተዓላ በሌላ የቁርዐኑ አንቀፅ ላይ እንዲህ ብሎ ገልፆታል፡-

«አላህ ለመኖሩ መጀመሪያም ሆነ መጨረሻ የለውም»

ቀለምንም ሰሌዳ ላይ ሁሉንም ነገር እንድትፅፍ አዘዛት ማለት አሏህ ለውሐል መህፉዝን ፈጠረ፤ ቀለምንም የፍጡራኖችን ፍርድ ሁላ እንድትፅፍ አዘዛት:: ከዚያም ሰማይና ምድርን ውስጧ ካሉት ጭምር በስድስት ቀን ፈጠረ::

## ሰማይና ምድር በስድስት ቀን የመፈጠራቸው ጥበብ

አሏህ በቁርዓኑ እንዲህ ብሏል፡-

وَلَقَدْ خَلَقْنَا السَّمَاوَاتِ وَالأَرض وَمَا بَيْنَهُمَا فِي
سِتَّةِ أَيَّامٍ وَمَا مَسَّنَا مِنْ لُغُوبٍ"



Scanned by CamScanner

# ኢስራዕና ሚዕራጅ

## የኢስራዕ ጆግራፊያዊ አቀማመጥ

የለሊት ጉዟቸው ከመካ እንስቶ መዲነቱል ሙነወራ፣ ጡሪሲና እና በይቱ-ለህምን አልፈው ፊሊስጢን ውስጥ በሚገኘው ቁድስ አብቅቷል፡፡
መካና መዲና በመካከለኛ ምዕራብ የአረብ ግዛት ውስጥ ቀይ ባህር አካባቢ የሚገኙ ሲሆን ጡሩ ሲናእ በደቡብ በኩል የሚገኘው የሲናእ በረሀ አካባቢ ነው፤ በይቱለህም በፊሊስጢን ውስጥ ከቁድስ የደቡብ አቅጣጫን ይዞ ይገኛል፡፡

## የኢስራእ ታሪክ

የኢስራዕ ሙዕጂዛ በቁርዓንና በሀዲስ የተረጋገጠ በመሆኑ አላህ ነብያችን ሙሀመድን ከተከበረችው መካ እስከ መስጂደል አቅሷ የለሊት ጉዞ እንዳስደረጋቸው የማመን ግዴታ አለብን።
የሀቅ ባለቤቶችም(ምሁራን) ይህ ጉዞ በአካላቸውና በሩሃቸው ንቃት ላይ ሆነው እንደተከሰተ ይስማማሉ፡፡ ስለሆነም ዑለማኦች "ኢስራእን የሚክድ ቁርአንን ያስዋሸ ይሆናል፤ ቁርዐንን የሚያስዋሽ ከእስልምና ይወጣል" በማለት ተናግረዋል፡፡
ረሱል ፋኺታ ቢንት አቢጧሊብ «ኡሙ ሀኒዕ» በመባል የምትጠራው የአጎታቸው ልጅ ዘንድ ተኝተው የነበረ ሲሆን ጂብሪል አለይሂ ሰላም ጣራውን ቀዶ በመምጣት ወሰዳቸው፡፡
በማሊክ ረዲየላሁ ዐንሁ ዘገባ በማሊክ ቢን ሰዕሰዕ ሀዲስ ነብያችን ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

በወርቅ ሳህን ኢማን ተሞልቶ መጥቶ ልቤ ከታጠበ በኋላ ወደ ቦታው ተመለሰ»

ይህንን አስመልክቶ ነወዊይ ረዲየላሁ ዐንሁ «ሳህኑ ውስጥ የነበረው ኢማንና ሒክማ(ጥበብን) ሙሉ የሚያደርግ ነው፡፡» ብለዋል
በይሐቂይ ረዲየላሁ ዐንሁ ከሸዳድ ቢን አውስ እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፡-
«ያረሱለላህ! እንዴት ነበር የለሊት ጉዞዎ?» በማለት ጠየቅናቸው፡፡

እርሳቸውም« ሶላቱል ዐትማ ሰገድኩኝ! ጂብሪልም ከአህያ ከፍ ያለች ከበቅሎ አነስ ያለች እንስሳ አምጥቶ ‹ ውጣ › አለኝ፡፡ መውጣቱ ሲከብደኝ የእንስሳዋን ጆሮ ይዞ ካዞራት በኋላ እንድወጣ ረዳኝ፡፡ የእንስሳዋ እርምጃ አይን የምታየውን ርቀት ያህል ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ እየተጓዝን ቴምር የበዛበት ምድር ስንደርስ ‹ውረድ› አለኝ፡፡ ወረድኩ፤‹ስገድ› አለኝ ሰገድኩና ተመልሰን ወደ እንስሳዋ ወጣን፡፡ ‹የት እንደሰገድክ ታውቃለህ?› ብሎ ጠየቀኝ፤ ‹አላሁ አዕለም› ብዬ መለስኩ፡፡ ‹የስሪብ ይባላል› አለኝ፡፡ ጠይባም ላይ ሰገድኩኝ፤እንስሳዋ በአይን እይታ ያህል እየተራመደች አንድ መሬት ስንደርስ ጂብሪል ‹ውረድ› አለኝ፡፡ ወረድኩ፤‹ስገድ› አለኝ ሰገድኩና ተመልሰን ወደ እንስሳዋ ወጣን፡፡ ‹የት እንደሰገድክ ታውቃለህ?› ብሎ ጠየቀኝ፤ ‹አላሁ አዕለም› ብዬ መለስኩ፡፡ ‹ሙሳ አለይሂ ሶላቱ ወሰላም አላህን ያነጋገሩበት ጡሩ ሲናእ የሚባል ቦታ ነው› አለኝ፡፡ ከዚያም እንስሳዋ ለአይን እይታ በሚደርስ መልኩ እየተራመደች ትልልቅ ቤቶች የበዙበት ምድር ደረስን፡፡ ‹ውረድ› አለኝ፡፡ ወረድኩ፤‹ስገድ› አለኝ ሰገድኩና ተመልሰን ወደ እንስሳዋ ወጣን፡፡ ‹የት እንደሰገድክ ታውቃለህ?› ብሎ ጠየቀኝ፤ ‹አላሁ አዕለም› ብዬ መለስኩ፡፡ ‹የሰገድከው የመርየም ልጅ ዒሳ አለይሂ ሶላቱ ወሰላም የተወለዱበት በይቱ-ለህም የሚባል ቦታ ነው› አለኝ፡፡





Scanned by CamScanner

# ኢስቲንጃእ

- ያልተከበረ ነገር ሲባል ደግሞ ሸሪዓዊ ፅሁፍ ያለበት ወረቀትና የሚበላ ምግብ እንደዳቦ ያሉትን ለማለት ሲሆን በነዚህ ነገራቶች ኢስቲንጃእ ማድረጉ አይፈቀድም፡፡ድንጋይና የድንጋይን ምትክ በሚጠቀምበት ሰአትም ቢያንስ ሶስት ግዜና ከዛ በላይ መጥረግ ይኖርበታል፡፡ ነጃሳው በሶስት ካልተወገደ አራተኛ በአራት ካልተወገደ አምስተኛ..... መጨመሩ ግዴታ ሲሆን በነጠላ ቁጥር ማቆሙ ደግሞ ሱና ይሆንለታል፡፡

የተወደደው የኢስቲንጃእ አይነት መጀመሪያ በድንጋይ (የድንጋይ ምትክ እንደ ሶፍት) ነጃሳውን አስወግዶ በውሃ መታጠብ ሲሆን ከሁለቱ አንዱን ብቻ ማድረግም ይችላል፤ ውሃን መጠቀሙ ግን የተመረጠ ይሆናል፡፡ አንዳንድ ሰዎች በግራ እጅ ውሃ በመውሰድ ነጃሳው የወጣበት የሰውነት ክፍል የሚያጥቡት በጣም አፀያፊና ፈፅሞ ኢስቲንጃእ ሊባል የማይችል ድርጊት ሲሆን ትክክለኛው የኢስቲንጃእ አደራረግ ነጃሳው የወጣበት አካል ላይ ውሃን በቀኝ እጅ በማፍሰስ በግራ እጅ የተፀዳዳበትን የሰውነት ክፍል ነጃሳው ምልክቱን ጨምሮ እስኪወገድ ድረስ ማጠብ ነው፡፡

በምድረ-በዳ መሬት በሚፀዳዳበት ጊዜ በሽንትም ሆነ በሰገራ ወደ ቂብላ መዞሩ ሃራም ሲሆን ከፊት ለፊቱ ከፍታ ያለው ነገር ካስቀመጠ (2/3 ክንድ ወይም ከዚያ በላይ ከፍታ ያለውን ነገር ከራሱ ሶስት ክንድ በማይርቅበት ሁኔታ ካስቀመጠ) ሐራም አይሆንበትም፤ እንደዚሁም ለዚሁ አላማ ተብሎ የተዘጋጀ ቦታ ከሆነ (ሽንትቤት) ወደ ቂብላ ዞሮ መፀዳዳቱ ሃራም አይሆንም፡፡

## መፀዳዳት ከሚጠላባቸው ቦታዎች መካከል፡-

- ከሚያፈራ ዛፍ ስር መፀዳዳት፡- በሚያፈራበትም ወቅት ይሁን በሌላ ጊዜ ዛፍ ስር መፀዳዳት የተጠላ ይሆናል፤ ይህም ፍሬው ነጃሳ ላይ ወድቆ ነፍስያችን እንዳይጠላው ሲባል ነው፡፡ ይህ የሚሆነው የራሱ ዛፍ ሲሆን እንጂ የሌላ ሰው ዛፍ ከሆነ ባለቤቱን ሳያስፈቅድ መፀዳዳቱ ሀራም ይሆንበታል፡፡
- መንገድና ጥላ ስር መፀዳዳት፡- ይህም የተጠላው ድርጊት ፈፃሚውን ስለሚያስረግመው ነው፡፡ ነብያችን አለይሂ ሰላቱ ወሰላም ሙስሊም በዘገቡት ሃዲስ ‹‹ሁለት ከሚያስረግሙ ድርጊቶች ተቆጠቡ፤›› አሏቸው፤ የሚያስረግሙት ድርጊቶች እነማን ናቸው? ተብለውም ሲጠየቁ ‹‹ሰዎች በሚሄዱበት መንገድና ጥላ ስር መፀዳዳት ናቸው›› ብለዋል፡፡ በክረምት ፀሃይ የሚገኝበት ቦታዎች በበጋ እንደ ጥላ ቦታዎች የሚቆጠሩ ይሆናል፡፡
- በመሬት ላይ በሚገኝ ቀዳዳ መፀዳዳት፡- ቀዳዳው ትልቅ ይሁን ትንሽ፣ ጥልቀት ይኑረው አይኑረው ከመፀዳዳት ሊቆጠብ ይገባል፡፡ ይህም ቀዳዳው የእንስሳት ወይም የጅኖች መኖሪያ ሊሆን ስለሚችል ነው፡፡
- ሰገራም ሆነ ሽንት በሚፀዳዳበት ግዜ መነጋገር የተጠላ ሲሆን መስጂድ ውስጥ መሽናት በእቃም ቢሆን ሃራም ይሆናል፡፡
- ማንኛውም ሰው የአላህም ሆነ የመልከተኛው ስም የተፃፈበትን ነገር ይዞ ሽንት ቤት ከመግባት መቆጠብ ይኖርበታል፡፡

ሽንት ቤት መግባት የሚፈልግ ሰው፡- «አዑዙ ቢላህ፣ ቢስሚላህ፣ አላሁመ ኢኒ አኡዙ-ቢከ ሚነል ኹብሲ ወል ኸባኢስ» ማለቱ ይወደድለታል፡፡ይህም «በአላህ ስም ከወንድና ሴት ጅኖች እጠበቃለሁ» ማለት ነው፡፡ በሚገባበት ሰአት የግራ እግሩን በማስቀደም ሲወጣ ቀኙን ማስቀደሙ ሱና ይሆንለታል፡፡ ሲወጣም «አልሃምዱሊላህ አለዚ አዝሀበ አኒል አዛ ወአፋኒ» ማለቱ ይወደድለታል፡፡

***ማሳሰቢያ፡- ይህ የኢስቲንጃእ አህካሞች (ፍርዶች) የተገለፁት በኢማሙ ሻፊዒይ መዝሀብ መሰረት ነው፡፡***

# የሰውን ውዴታ እንዴት ታገኛለህ?

ሰዎች መሃከል ውዴታንና ተቀባይነት ማግኘት የበዙሃኑ ጥረት ነው። ይህንን ለማሳካት የተወሰኑ ነጥቦችን መከተል አስፈላጊ ነው። እነዚህም:-

## 1. ሰውን መቅረብ

አሳዛኝ ከሆኑ እውነታዎች ውስጥ አንዱ አንዳንድ ሰዎች ማንንም ሳይቀርቡ ሰዎች እንዲወዷቸው ይጠብቃሉ። ምናልባትም ሳልቀርባቸው እነሱ ይወዱኛል በማለትም የሚጎርፉ አይታጡም።

መልካም ሰዎችን መቅረብና በነሱ ለመወደድ መጣር አስፈላጊ ነገር ነው። በሃዲስም ከብቸኝነት ይልቅ ከሷሊህ ሰው ጋር መሆን፤ ከመጥፎ ሰው ጋር ከመሆን ብቸኝነት እንደሚሻል ተነግሯል።እድጉትን የፈለገ የምርጥና የመልካም ሰዎች ጓደኛ ይሁን። አንዳንድ ዑለማእች እንዲህ ብለዋል «አላህ አንድን ባሪያ የተቀይ ሰው ጓደኛ በመሆኑ ምክንያት ሊያዝንለት ይችላል»

## 2. ሰዎችን ማመስገን:-

ረሱል ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል «ሰውን ያላመሰገነ አላህን አላመሰገነም» ማለትም ሰውን ማመስገን ያለመደ ፈጣሪው በሰጠው ፀጋ ያመሰግናል ብሎ ማሰብ አዳጋች ይሆናል:: ሰውን ማመስገን የሚሆነው በመሸለም፣ ስጦታ በማበርከት፣ ዱዓእ በማድረግና በመሳሰሉት ይሆናል።

አቡበከር ሲዲቅ ረዲየላሁ ዐንሁን መልእከተኛው እስልምናን ከማስያዝ፤ እንዣር ትልቅ ውለታ የዋሉላቸው ቢሆንም እስልምናን ከተቀበሉ በኋላ ለሕዝበ-ሙስሊሙ ባደረጉት በርካታ ተግባሮቻቸው መልእከተኛው አመስግነዋቸዋል::

በእርግጥም! ከልብ የመነጨ እድናቆትና ምስጋና ተመስጋኙን ስላለው አስፈላጊነት እንዲሰማው ከማድረጉም ባሻገር በሰዎች መካከል ውዴታ እስገኝልናል::

Scanned by CamScanner

# ዑስማን ኢብኒ አፋን (ረዲየላሁአንሁ)

ዑመር ረዲየላሁ አንሁ ከሞቱ በኋላ በመሪነት ሲያስተዳድሩ የነበሩት ሌላኛው አንጋፋ ሶሀባ ዑስማን ኢብን አቡ አብዱላህ ቢኒ አቢ ዒሣ ቢኒ ኡመያህ በመባል ይታወቃሉ። እናታቸው አርዋ ቢንት ኩረይዝ ቢን ረቢዓህ ነበረች። ረሡል ሶለላሁ አለይሂ ወሡለም ከተወለዱበት አመል ፊል በመባል ከሚታወቀው ከ6 አመት በኋላ ተወለዱ። እስልምናን የተቀበሉት በ39 አመታቸው በአቡበከር ረዲየላሁ አንሁ አማካኝነት ነበር። ይህም ረሡል ሶለላሁ አለይሂ ወሡለም ዳሩል አርቃም ከመግባታቸው በፊት በመሆኑ ቁርአን ላይ ከተጠቀሡ ቀዳሚ ሡለምተኛ (እስልምናን ከተቀበሉ) አንዱ ሆነዋል። ከዚህም ባሻገር ረሡል ሡለላሁ አለይሂ ወሡለም 10 ሠዎችን የጀንት ብለው ካበሡሯቸው አንዱ መሆን ችለዋል።

በብዙ ነገራቶችም ቀዳሚ በመሆን ይታወቃሉ።። ለምሣሌ፡-

- ለመጀመሪያ ጊዜ ከነቤተሡቦቻቸው ሂጅራ ወደ ሀበሻ ማድረጋቸው
- መስጂድን በጥሩ መዓዛ ማወድን ማስጀመራቸው
- የጁምአ ሁለተኛ አዛንን ማስጨመራቸው
- ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙአዚን ደሞዝ ማስቆጠራቸው
- ለመጀመሪያ ጊዜ እናታቸው በህይወት እያሉ ኸሊፋ በመሆናቸው

ዑስማን ረዲየላሁ አንሁ እንደ አቡበከርና ዑመር ከረሡል ሶላላሁ አለይሂ ወሡለም ጋር በመሆን ሁሉንም ጦርነቶች ተካፍለዋል። ነገር ግን በበድር ጦርነት ላይ ባለቤታቸው ሩቂያህ (የረሡል ሶላላሁ አለይሂ ወሡለም ልጅ) በህመም ላይ ስለነበረች በረሡል ሡላላሁ አለይሂ ወሡለም ትዕዛዝ ጦርነቱን መካፈል አልቻሉም። ነገር ግን ረሡል ሡላላሁ አለይሂ ወሡለም ጦርነቱ ላይ እንደተካፈሉ በመቁጠር በጦርነቱ የተገኘውን ውርስ አካፍለዋቸው ነበር።

ነብዩ ሙሐመድ ሶላላሁ አለይሂ ወሡለም ወህይ ሣይወርድላቸው በፊት ልጃቸውን ሩቀያን ለሡይዱና ዑስማን ድረውላቸው ነበር። በመሆኑም ወደሀበሻ ባደረጉት ጉዞ አብራቸው ተጉዛለች። ያረፈችውም የበድር ጦረነት በተካሄደባቸው ለሊቶች ሲሆን ከመሞቷ በፊት ግን አብዱላህ የተባለ ልጅ ወልዳላቸው ነበር። በዚህም የተነሣ አቢ-አምር ተብለው ይጠሩበት የነበረው ስማቸው አቢ አብዲላህ እንዲባሉ ምክንያት ሆኗል። ሩቀያ ከሞተች በኋላ ረሡል ሶላላሁ አለይሂ ወሡለም ኡምኩልሱም የተባለች ልጃቸውን ዳሩላቸው።። በሒጅራ አቆጣጠር እስከ ዘጠነኛ አመት አብረው ቢኖሩም በድጋሚ በሞት ተለያቻቸው። ስለሆነም ዚኑረይን (የሁለት ብርሀን ባለቤቶች) ለመባል ችለዋል።

# ዑስማን ኢብኒ አፋን (ረዲየላሁአንሁ)

የኡስራ ጦር ሠራዊት ያዘጋጁትም ቲርሚዚይ ከአብዱራህማን ቢን ኸባብ እንዲህ ማለታቸውን ዘግበዋል "ረሡል ሶለላሁ አለይሂ ወሠለም ለኡስራ ጦርነት የሚሆን የገቢ ማሰባሰቢያ ንግግር እያደረጉ ሣለ ዑስማን ረዲየላሁ ዐንሁ እንዲህ አሉ " 100 ግመል ከነምግቡና አስፈላጊ ነገራቶችን ከማሟላት ጋር አቀርባለሁ " ረሡልም ተመልሰው ሠዎችን ለማነሣሣት ንግግር ሲያደርጉ "ሌላ ሁሉንም ነገር ያሟላ 100 ግመል እችላለሁ" በማለት ዑስማን ተናገሩ ይህን ጊዜ መልእክተኛው አለይሒ ሶላቱ ወሰላም እጃቸውን እያነቃነቁ "ከዚህ በኃላ ዑስማን ምንም ቢያደርጉ የጀነት ሰው ናቸው " በማለት ተናገሩ፡፡

## ቁርአንን ስለመሠብሠባቸው

ረሡል ሶለላሁ አለይሂ ወሠለም ሞተው አቡበከር ረዲየላሁ ዐንሁ ኸሊፋ ሣሉ ብዙ የቁርአን ሀፊዞች በጦርነት ሠበብ መሞታቸውን አቡበከር ረዲየላሁ ዐንሁ በማስተዋል ወህዩን ይፅፉ የነበሩ ዘይድ ኢብኑ ሣቢት የተባሉ ሠሀቢይን በማስጠራት ቁርአን በፅሁፍ መልክ እንዲሠበሠብ ሀሣብ አቀረቡላቸው።

ዘይድ ግን ረሡል ሶለላሁ አለይሂ ወሠለም «ያላደረጉትን እንዴት እናደርጋለን?» በማለት ጠየቁ ይህን ጊዜ ዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ ስለሀሣቡ ጥሩነትና ሸሪዓን እንደማይቃወም አስረዷቸው። ቁርዓኑንም መሠብሠብ ተጀመረ በዚህ መሀከል አቡበከር ህይወታቸው አለፈ። አቡበከር ሞተው ዑመር ረዲየላሁ አንሁ ሲተኩም መሠብሠቡ ቀጠለ። ዑመርም በአንድ ሙስሀፍ ተሠብሥቦ ከማለቁ በፊት ህይወታቸው አለፈ። በዚህ ጊዜ ዑስማን ረዲየላሁ ዐንሁ ኸሊፋ ሆነው ማስተዳደር ጀመሩ። የተሠበሠበው ቁርዐንም የዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ ልጅ ሀፍሣ ዘንድ ተቀመጠ።

በዑስማን ዘመን ሠዎች በቁርዐን አቀራር ስልት መጣላትና ኺላፍ(ልዩነት) እየበዛ ሲመጣ ዑስማን ረዲየላሁ ዐንሁ ይህ ኺላፍ የባሰ ደረጃ እንዳይደርስ ስለስጉ 12 ሶሀባዎችን በመሠብሠብ አማከሯቸው። ከተሰበሰቡት መሐከል ለረሡል ሶለላሁ አለይሂ ወሠለም ይወርድላቸው የነበረውን ወህይ የሚፅፍ ሶሀባ ነበር። የዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ ልጅ የሆነችው ሀፍሣ ዘንድም ዘይድ ኢብኒ ሣቢት የሠበሠቡትን ቁርዐን እንድትልክ አዘዟት። "ፈትሁል ባሪ" በተባለ የኢብኑ ሀጀር አል አስቀላኒይ ኪታብ ላይ እንደተጠቀሰው:- ዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ "ማን ይሆን ከናንተ መሀከል ጥሩ ፀሀፊ ?" በማለት ጠየቁ፤ እነሡም "ዘይድ ኢብኑ ሣቢት" በማለት መለሡ፤ በድጋሚ "ማን ነው ከሁላችሁ ጥሩ ቃሪእ(አንባቢ)?" በማለት ጠየቋቸው። እነሡም "ሰዒድ ኢብኑ ዒሳ" ብለው መለሡ፤ ይህን ጊዜ "ሰዒድ እየቀራ ዘይድ ከስሩ ይፃፍ" በማለት ተዕዛዝ አስተላለፉ።

Scanned by CamScanner

# ዑስማን ኢብኒ አፋን (ረዲየላሁአንሁ)

## ሠዎች ስለ ዑስማን ኢብኑ ዐፋን የነበራቸው አስተያየት

ኢማም አህመድ እንደዘገቡት ሩሀይማ የተባለች የዙበይር ቢን አብዱላህ አያት የሆነችው እንዲህ በማለት ተናግራለች:- "ዑስማን አመቱን በሙሉ ይፆሙ ነበር፤ ለሊቱንም በመስገድ ያሣልፉ ነበር"

ኢብኑ አሣኪር ባስተላለፉት ንግግር አብዱራህማን ኢብኑ ሙህዲይ እንዲህ በማለት ተናግረዋል:- "ሁለት ነገራቶች አቡበከርም ሆነ ዑመር ሣይኖራቸው ዑስማን ረዲየላሁ ዐንሁ ግን አላቸው፤ የመጀመሪያው በበደል ሲገደሉ የነበራቸው ሶብር

## የነበራቸው መተናነስ



ሠይዱና ዑስማን ረዲየላሁ ዐንሁ የስነ-ምግባር አርአያነታቸው፣ በጥሩ ባህሪያቸው፣ በጥበበኛነታቸው፣ በቸርነታቸው፣ በልበ-ንፁህነታቸው፣ በጥንቁቅነታቸው እና በዙህዳቸው (ለአዱንያ ባለመጨነቃቸው) ከመታወቃቸውም ባሻገር የነበራቸው መተናነስ ይበልጥ ጎልቶ ይታይ ነበር::

ኢብኑ ሠዒድ ከአብዱላህ አሩሚይ እንደዘገቡት ዑስማን ረዲየላሁ ዐንሁ ለሊት ለዉዱእ የሚሆን ዉሀ ራሣቸው ነበር የሚቀዱት፤ አንድ ቀን ‹ለምን ኻዲሞችን አታዙም?› ተብለው ሲጠየቁ ‹ይህ የዕረፍት ጊዜያቸው ነው› በማለት መለሱ::

ኢማም አህመድ እንደዘገቡት ኢማም ሀሠን ረዲየላሁ አንሁ በቀን መስጂድ ውስጥ ስለሚተኙትና ስለሚያሸልቡት ሲጠየቁ "ዑስማንኸሊፋ በነበሩበት ዘመን እንኳ መስጂድ ውስጥ በሠውነታቸው ላይ ምልክት እስኪወጣ ድረስ ጋደም ይሉ ነበር:: ሠዎችም እያዩዋቸው ‹ይህኮ አሚረል ሙዕሚኒን ነው› በማለት ይጠቋቀሙባቸው ነበር::"

ሹራቢል ቢን ሙስሊም እንደተናገሩት "ዑስማን ረዲየላሁ ዐንሁ ሠዎችን የነገስታት ምግብ ይመግቧቸውና ለራሣቸው ቤታቸው ገብተው የሚበሉት ዘይትና ቆምጣጤ ነበር::"

## ስለኸሊፋነታቸው

በ23ኛው አመተ-ሒጅራ በዙል-ሒጃ ወር ማገባደጃ ዑመር ኢብን አል-ኸጧብ አረፉ፤ ከሶስት ቀናት በኃላ ማለትም በዕለተ ሰኞ የዙል-ሒጃ ወር ሊቋጭ አንድ ቀን ሲቀረው ሠይዳችን ዑስማን ኢብን ዐፋን የሙስሊሞች መሪ (ኸሊፋ) እንዲሆኑ ስምምነት ላይ ተደረሰ:: ታድያ 24ኛውን አመተ-ሒጅራ አዲስ አመት (ሙሀረም) ትልቁን አደራ ተቀበሉ:: ይህንንም አደራ ጠብቀው ለ12 አመታት ቆዩ:: በመሪነታቸው ዘመን እንደ አቡበከር እና ዑመር ረዲየላሁ ዐንሁ የነብዩን ሶለላሁ አለይሒ ወሰለም ቀለበት ያደርጉ ነበር:: እንደዚያውም በርካታ ሀገራትን በኢስላማዊ አገዛዝ ስርዐት እንዲካተቱ አድርገዋል:: ከነዚህም ድል ከተጎናፀፉባቸው ሐገራት መካከል:- ቆጥሮስ ደሴት፣ከርማን፣ሲጂስታን፣ካቡል እና ሌሎች የአፍሪካ ሐገራት ተጠቃሾች ናቸው::



Scanned by CamScanner

# ዑስማን ኢብኒ አፋን (ረዲየላሁአንሁ)

## አማሟታቸው

ፈትህ የሚደረጉ ሀገራት ( ኢስላም ድል ያደረጋቸው ሀገራት) ሲበዙ፤ ከመካና መዲና ውጪ ያሉ ከተሞች ላይ ግዛቱ ሲጠናከር፤ አረቦች ከሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ሠዎች ጋር ሲቀላቀሉ፤ መሠረት የሌላቸው ወሬዎች መዲና ላይ ሲሠራጩ፤ የዑስማን ረዲየላሁ ዐንሁ ተቃዋሚዎች ባገኙት አጋጣሚ ከመዲና ውጪ ለሚገኙት መሠል ተቃዋሚዎች ዑስማን ረዲየላሁ ዐንሁን ከስልጣን ማውረድ እንዳለባቸው መልእክት ላኩ። በዚህን ጊዜ እርሣቸውን ለመግደል ለተወሠኑ ቀናት ቤታቸውን ከበው ቆዩ።



የጥላቻቸው ብዛት ውሃ እንኳን እንዲሠጣቸው ፈቃደኛ አልነበሩም። አሊይ ረዲየላሁ አንሁ ይህንን በሠሙ ጊዜ በሦስት ትላልቅ ዕቃዎች ውሀ ሞልተው፤ ላኳቸው። ነገር ግን ማሻአላሁ ካን (አላህ መከሠቱን የፈለገው መከሠቱ አይቀርምና) ሦስት ሠዎች በአንድ አንሷሪይ ቤት በጀርባ በኩል በመግባት ፆመኛ ሆነው ቁርአን በመቅራት ላይ የነበሩትን ሦስተኛ ኸሊፋ ከጀርባቸው ለመግደል ሠይፋን ሲሰነዝር ቤት ውስጥ ለብቻዋ የነበረችው ሚስታቸው ለመከላከል ሞከረች። በዚህን ጊዜ የእጆቿ ጣቶች ተቆረጡ ሆኖም ከመገደል አላዳነቻቸውም። ዑስማን ረዲየላሁ ዐንሁ በ90 አመታቸው በጁምዓ ቀን ሸሂድ ሆነው ተገደሉ። ቅዳሜ በመግሪብና በኢሻዕ መካከል በመዲና ከተማ በቂእ ተብሎ በሚጠራው የቀብር ስፍራ ዙበይር አሠግዶባቸው ተቀበሩ።

ዑስማን ረዲየላሁ ዐንሁ ከመገደላቸው በፊት "ትላንት በህልሜ ረሡልን ሠለላሁ አለይሂ ወሠለምና አቡበከርን 'ሶብር አድርግ ነገ ከኛጋር ነው የምታፈጥረው ' ሲሉኝ አየኋቸው" በማለት ተናግረዋል።

ረሡል ሠለላሁ አለይሂ ወሠለም ለዑስማን "ሙናፊቆች ኸሊፋ በምትሆንበት ዘመን ሊያወርዱህ ይጥራሉ፤ ነገርግን አትወርድላቸውም እኔን እስከታገኘኝ ድረስ" ማለታቸውን አኢሻ ተናግራለች።



Scanned by CamScanner



# ጊዜን በአግባቡ መጠቀም

## *አንተ አንባቢ ሆይ!...... አንቺ አንባቢ ሆይ!......እንደ ጊዜ ጥብቅ ሁን/ሁኚ!!!*

አዎን! ጊዜ እንደ ተንጠለጠለ ጎራዴ ነው፤ ቀድመህ ካልቆረጥከው ይቆርጥሃል፤ ቁም ነገር ላይ ካላዋልከው ያመልጥሃል፡፡

ጊዜ እንደ እንቁ በጣም ውድ የሆነ ሲሆን አሏህ ባዘዘን ነገር ካላሳለፍነው ምንም አይነት ጥቅም አይኖረውም፡፡

ጊዜያችንን አሏህ ሱብሃነሁ ወተዓላን በመታዘዝ ማሳለፍ እንጂ እሱ ባደረገልን ፀጋ ተዘናግተንና ግዜ አጥተን ዋና አላማችንን መርሳት አይኖርብንም፡፡ የጊዜን በረካ ልናገኝ የምንችለው ደግሞ ጊዜያችንን ጠቃሚ ለሆኑ ነገራት በአግባቡ በመከፋፈል ሲሆን ይህም አላህ ለፈቀደውና ለወደደው ነገራት እንደየ-አስፈላጊነቱ ቅድሚያ በመስጠት ለምግብም ሆነ ለመጠጥ፤ ለእንቅልፍም ሆነ ለእረፍት፤ ለአካላዊ እንቅስቃሴ፤ ተፈጥሮን ለማድነቅ፤ አላማ ላለው መዝናናት፤ ለመማር፤ ለመስራት፤ ለንግድ፤ ለጓደኛ፤ ለዘመድ፤ ለቤተሰብ፤ ለእናት አባት፤ ለልጆች፤ ለሚስት በማለት አስበንና አቅደን በመከፋፈል ማስተዳደር ስንችል ነው፡፡

Scanned by CamScanner

## ስድስት አይነት ወንዶችን ከማግባት ተጠንቀቂ



1. ውሸታም፡- ውሸት የሚያበዛና ከተከሰተው ነገር ውጭ የሚያወራ ሲሆን በመሃከላቸው ያለውን ግንኙነት እምነትን በማጥፋት ያሻክረዋል
2. ተማቺ፡- ሚስቱን ምት በማብዛት አካሏን የሚጎዳ
3. አጭበርባሪ፤- ማታለልና ማምታታት የሚያበዛ ሲሆን ላለ-አስፈላጊ መረበሽና ጭንቀት ይዳርጋል
4. ተሳዳቢ፡- ስድብና መጥፎ ቃላትን በመሰንዘር ሚስቱን የሚያስከፋና የሚጎዳ
5. ትችተኛ፡- ምንም ቢደረግለት የማያስደስተው፤ መልካም ነገሮችን ትቶ ሁልግዜ ከፋውን ብቻ በመቁጠር ወቀሳና ነቀፌታ የሚያበዛ
6. እንቅልፋም፡- እንቅልፍ ከማብዛቱ የተነሳ ሰላቱን የሚተው፤ በጠዋት ሪዝቁን ለመፈለግና እድሜውን በአግባቡ ለመጠቀም ጥረት የማያደርግ

## ስድስት አይነት ሴቶችን ከማግባት ተጠንቀቂ



1. ነጭናጫ፡- ፍላጎቷ ገደብ የሌለው፤በትንሽ የማትብቃቃ የምቾት ኑሮ በመፈለግ ሁል ግዜ መነጫነጭ የምታበዛ
2. የምታማርር፡-ያለፈውን የትዳር ህይወትና የጓደኞቿን ኑሮ በመመልከት የአንተንና የቤተሰቦችህን ሁኔታ የምታማርር
3. ተመፃዳቂ፡- የአንተን ልቦና ለመስበር ብላ ያደረገችልህን ውለታ የምትቆጥርና ራሷን ከፍ ከፍ የምታደርግ
4. የሰውን መመልከት የምታበዛ፡- በልብስ፤ በንብረትም ሆነ በቁሳቁስ የሌላውን ብቻ ተመልከታ በገበያና በሱቆች መስኮት ላይ የምታንጋጥጥ፤ ምንም ቢደረግላት የማትጠግብ
5. የምታብረቀርቅ፡- በአንተና በቤትህ ወጪ በጣም ለሚታዩ ነገራት የምትጨነቅና ለአንተ ሳይሆን ለራሷ በጣም መጋጌጥ የምትወድ
6. ወረኛ፡- ምንም ጥቅምና ኸይር የማይገኝበት ንግግር በማብዛት ከሷ አልፎ ለአንተም ጭምር ችግር የምታስከትል

Scanned by CamScanner

# የምስር ሾርባ







<u>አስፈላጊ ግብአቶች</u>

- ½ ኪሎ ምስር
- 3 ትላልቅ ራስ ሽንኩርት
- 1 ማንኪያ የተፈጨ ነጭ ሽንኩርት
- 1 የሻይ ማንኪያ የተፈጨ ከሙን
- ጨውና ቆንዶ በርበሬ ለጣእም
- ሎሚ
- ዘይት

<u>አዘገጃጀት</u>፡- ምስሩን አጥቦ በደንብ እስኪበስል መቀቀል፤ በሌላ መጥበሻ ዘይት አሙቅን ሽንኩርቱን ወርቃማ እስኪሆንመጥበስ፤ አስከትሎ ነጭ ሽንኩርቱን ጨምሮ ወዲያው ወደ ምስሩ መደባለቅ፤ ከሙን፤ ጨውና ቆንዶበርበሬውን እንደፍላጎታችን ጨምረን ለሁለት ደቂቃ በማማሰል ከግማሽ ሎሚ ጋር ትኩሱን ማቅረብ!

Scanned by CamScanner



# ለህፃናት

## ቅደም ተከተል ጠብቀህ ሳል






Scanned by CamScanner

# እንቆቅልሽ

1. ለማገዶ የማይውል ጭራሮ
2. ወደ ላይ ከወጣ የማይመለስ
3. ጥርስ የላት ጥሬ መብላት አያቅታት
4. የሚልተውብት ወዲያው ባዶ
5. እቴ ድቡልቡል ሸከርከር ነፍስ ያለው ይወልድ ባለ እግር
6. ላጤ ጋለሞታ እናቷን ትመታ

## የሂፍዝ ዚክር

### ከምግብ በፊት የሚደረግ ዱዓእ

«አላሁመ ባሪክ ለና ፊማ ረዘቅተና ወእንተ ኸይሩ ራዚቂን ወእንተ ሐስቡና ወኒእመል ወኪል»

Scanned by CamScanner

የመጀመሪያው ፍጡር ምንድ ነው? 1

ኢስራዕና ሚዕራጅ 3

ኢስቲንጃእ 6

የኮምጣጤ ጥቂት ጥቅሞች 8

ይህን ያውቁ ኖሯል? 9

የስግብግብነት ውጤት 10

የስልጣን ውዴታም....ለህልፈት ይዳርጋል 10

የሰውን ውዴታ እንዴት ታገኛለህ? 11

ዑስማን ኢብኒ አፉን(ረዲየላሁአንሁ) 12

ጊዜን በአግባቡ መጠቀም 17

ስድስት አይነት ወንዶችን ተጠንቀቂ 18

ስድስት አይነት ሴቶችን ከማግባት ተጠንቀቅ 18

የምስር ሾርባ 19

ለህፃናት 20

ታሪክ አባ ዘር እንዴት ሰለሙ 21

እንቆቅልሽ 22

የሂፍዝ ዚክር 22

Scanned by CamScanner

عز الدين علي

ኢስራእ እና ሚዕራጅ

الإسـراء والمعـراج

دَلِيلُ النُّبُوَّةِ

# የነቢይነት መገለጫ ነው

EITA

www.eitamarkaz.org fb.com/eitamarkaz

Dua Printing Sh. Co.

Scanned by CamScanner